ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ ሻዕባን 1/1443 ሂ.
የአውቃፍ ሚኒስቴር ማርች 4/2022 ግ.

## ዘካና ተራ ምጽዋቶች በማህበራዊ ልማት ያላቸው ሚና

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{وَأَقِيمُوا الصَّلَاةَ وَآتُوا الزَّكَاةَ وَارْكَعُوا مَعَ الرَّاكِعِينَ}

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአንቀጹዋ ትርጉም፡
(ሶላትንም ደንቡን ጠብቃችሁ ስገዱ፡፡ ዘካንም (ግዴታ ምጽዋትን) ስጡ፡፡ (ለጌታችሁ) ከአጎንባሾች ጋርም አጎንብሱ፡፡) ማለት ይሆናል፡፡

አጋር የሌለው ብቸኛ አላህ እንጅ የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመስክራለሁ፡፡ ሰይዳችንና ነብያችን ሙሐመድ የእሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! የምህረት እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካሙ መንገድ ለተከተሏቸው አውርድ፡፡

ከዚህም በመቀጠል፡
የእስልምና እምነት ህግ ሰዎች የሚመሩበት መሰረቱ መተዛዘን፣ መተሳሰርና መደጋገፍ የሆነ ቅን ማህበራዊ ስርአት አስቀምጧል፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (በመዋደድ፣ በመተዛዘንና በመደጋገፍ የምእምናን ምሳሌ አንዱ አካል ህመም በሚሰማው ወቅት ሌሎች አካላት ተመሳሳይ የእንቅልፍ ማጣትና ህመም ስሜት እንደሚሰማቸው የአንድ ሰውነት አአካላት ነው)፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በሌላ ሐዲስ እንድህ ይላሉ፡ (አሽዓራዊያን በዘመቻ ወቅት ስንቃቸው በተጓደለ ጊዜ ወይም በመዲና የልጆቻቸው ቀለብ በአነሰ ጊዜ ያላቸው ሁሉ በአንድ ጨርቅ ያከማቹና በአንድ እቃ እኩል ይካፈሉታል፡፡ እነሱ ከኔ ወገን ናቸው፡፡ እኔም ከእነሱ ወገን ነኝ)፡፡

ለዚህም ነው የእስልምና ሃይማት ዘካን የግዴታ ምጽዋትና የመዋቅሩ ማእዘን ያደረገው፡፡ እንድሁም እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ወገኖች ፍላጎት በማሟላትና ጭንቃቸውን በማቃለል ጉልህ ሚና ይኖረው ዘንድ ምጽዋት እንድንሰጥ የሚገፋፋን ሲሆን ከበጎ ሥራ በሮችም ታላቁ መሆኑን አስገንዝቧል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{ خُذْ مِنْ أَمْوَالِهِمْ صَدَقَةً تُطَهِّرُهُمْ وَتُزَكِّيهِمْ بِهَا }

(ከገንዘቦቻቸው ስትኾን በእርሷ የምታጠራቸውና የምታፋፋቸው የኾነችን ምጽዋት ያዝ፡፡) እንድሁም እንድህ ይላል፡

{وَمَا أَنْفَقْتُمْ مِنْ شَيْءٍ فَهُوَ يُخْلِفُهُ وَهُوَ خَيْرُ الرَّازِقِينَ}

(ከማንኛውም ነገር የምትለግሱትን እርሱ ይተካዋል፡፡ እርሱም ከሲሳይ ሰጪዎች ሁሉ በላጭ ነው» በላቸው፡፡)

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (እስልምና በአምስት ማእዘናት ተዋቅሯል፡፡ ከአላህ በስተቀር የሚገዙት እንደሌለና ሙሐመድ የአላህ መልእክተኛ በመሆናቸው መመስከር፡፡ ሶላትን ደንቡን ጠብቆ መስገድ፡፡ ዘካን መስጠት፡፡ ሐጅን ማድረስ፡፡ ረመዳንን መጾም የሚሉት ናቸው)፡፡

ቅዱስ ቁርአንን ጠለቅ ብሎ የሚመራመር ሰው አላህ (ዐ.ወ.) በበርካታ ቦታዎች ዘካን ከግዴታዎች ሁሉ በጣም ታላቅ፣ የላቀና ከፍተኛ ቦታ ካለው ግዴታ ከሶላት ጋር የሚያቆራኘው መሆኑን ሊገነዘብ ይችላል፡፡ ይህውም የዘካ ደረጃ ከፍተኛ መሆኑን ለመግለጽና ሰዎችም እንድፈጽሙት ለገፋፋት ነው፡፡ አላህ (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{وَأَقِيمُوا الصَّلاَةَ وَآتُواْ الزَّكَاةَ وَمَا تُقَدِّمُواْ لأَنفُسِكُم مِّنْ خَيْرٍ تَجِدُوهُ عِندَ اللّهِ إِنَّ اللّهَ بِمَا تَعْمَلُونَ بَصِيرٌ }**

(ሶላትንም አስተካክላችሁ ስገዱ:: ዘካንም ስጡ:: ለነፍሶቻችሁም ከበጎ ሥራ የምታስቀድሙትን አላህ ዘንድ ታገኙታላችሁ:: አላህ የምትሠሩትን ሁሉ ተመልካች ነውና::) እንድሁም እንድህ ይላል፡

**{الَّذِينَ يُقِيمُونَ الصَّلَاةَ وَيُؤْتُونَ الزَّكَاةَ وَهُم بِالْآخِرَةِ هُمْ يُوقِنُونَ}**

(ለእነዚያ ሶላትን አስተካክለው ለሚያደርሱት፣ ዘካንም ለሚሰጡት፣ እነርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም እነርሱ የሚያረጋግጡ ለሆኑት::) አሁንም በሌላ አንቀጽ አንድህ ይላል፡

**{وَلَا يَحْسَبَنَّ الَّذِينَ يَبْخَلُونَ بِمَا آتَاهُمُ اللَّهُ مِن فَضْلِهِ هُوَ خَيْرًا لَّهُم بَلْ هُوَ شَرٌّ لَّهُمْ سَيُطَوَّقُونَ مَا بَخِلُوا بِهِ يَوْمَ الْقِيَامَةِ وَلِلَّهِ مِيرَاثُ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَاللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ خَبِيرٌ}**

(እነዚያም አላህ ከችሮታው በሰጣቸው ገንዘብ የሚነፍጉ እርሱ ለእነሱ ደግ አይምሰላቸው:: ይልቁንም፤ እርሱ ለነሱ መጥፎ ነው:: ያንን በርሱ የነፈጉበትን በትንሣኤ ቀን (እባብ ኾኖ) ይጠለቃሉ:: የሰማያትና የምድርም ውርስ ለአላህ ብቻ ነው:: አላህም በሚሠሩት ሁሉ ውስጥ ዐዋቂ ነው::) አሁንም እንድህ ይላል፡

**{ وَالَّذِينَ يَكْنِزُونَ الذَّهَبَ وَالْفِضَّةَ وَلَا يُنفِقُونَهَا فِي سَبِيلِ اللَّهِ فَبَشِّرْهُم بِعَذَابٍ أَلِيمٍ * يَوْمَ يُحْمَىٰ عَلَيْهَا فِي نَارِ جَهَنَّمَ فَتُكْوَىٰ بِهَا جِبَاهُهُمْ وَجُنُوبُهُمْ وَظُهُورُهُمْ هَٰذَا مَا كَنَزْتُمْ لِأَنفُسِكُمْ فَذُوقُوا مَا كُنتُمْ تَكْنِزُونَ }**

(እነዚያንም ወርቅንና ብርን የሚያደልቡትን በአላህም መንገድ ላይ የማያወጧትን በአሳማሚ ቅጣት አብስራቸው:: በርሷ ላይ በገሀነም እሳት ውስጥ በሚጋልባትና ግንባሮቻቸውም፣ ጎኖቻቸውም፣ ጀርባዎቻቸውም በርሷ በሚተኮሱ ቀን (አሳማሚ በኾነ ቅጣት አብስራቸው):: ይህ ለነፍሶቻችሁ ያደለባችሁት ነው:: ታደልቡት የነበራችሁትንም ቅመሱ (ይባላሉ)::)

(ከርሳቸው አላህ ይውደድና አብደላህ ቢን አባስ እንድህ ይላሉ፡ ‹ሦስት የተከበረው ቁርኣን አንቀጾች ከሦስት ነገሮች ጋር ተቀናጅተዋል፡፡ አንደኛዋም ያለመቀናጀዋ ተቀባይነት እይኖራትም፡፡

**وَ{أَطِيعُوا اللَّهَ وَأَطِيعُوا الرَّسُول}**

(አላህንም ተገዙ፤ መልክተኛውንም ታዘዙ፡፡) አላህን የታዘዘና ለነብዩ ያልታዘዘ ሥራው ተቀባይነት የለውም፡፡

**{وَأَقِيمُوا الصَّلاَةَ وَآتُوا الزَّكَاةَ}**

(ሶላትንም ደንቡን ጠብቃችሁ ስገዱ፡፡ ዘካንም (ግዴታ ምጽዋትን) ስጡ፡፡) ሶላትን የሚሰግድ ዘካን የማይሰጥ ከሆነ ሥራው ተቀባይነት የለውም፡፡

**{أَنِ اشْكُرْ لِي وَلِوَالِدَيْكَ}**

(ለኔም ለወላጆችህም አመስግን በማለት አዘዝነው)፡፡ አላህን ያመሰገነ ወላጆቹን የማያመሰግን ከሆነ ሥራው ተቀባይነት የለውም፡፡›

ተራ ምጽዋቶች ማህበራዊ ሚናውን እውን በማድረግ ረገድ ዘካን የሚደጉሙ መሆናቸው ጥርጥር የለበትም፡፡ ለዚህም ነው ወደአውነት አዘንባይ የሆነው የእስልምና ህግ እሱን እንድንፈጽም የሚገፋፋና የሚጎተጉተን፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (በገንዘብ ላይኮ ከዘካ ሌላም መብት አለበት) ካሉ በኋላ የምትከተላውን አንቀጽ አነበቡ፡፡

**{لَيْسَ الْبِرَّ أَنْ تُوَلُّوا وُجُوهَكُمْ قِبَلَ الْمَشْرِقِ وَالْمَغْرِبِ وَلَكِنَّ الْبِرَّ مَنْ آمَنَ بِاللَّهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِ وَالْمَلَائِكَةِ وَالْكِتَابِ وَالنَّبِيِّينَ وَآتَى الْمَالَ عَلَى حُبِّهِ ذَوِي الْقُرْبَى وَالْيَتَامَى وَالْمَسَاكِينَ وَابْنَ السَّبِيلِ وَالسَّائِلِينَ وَفِي الرِّقَابِ...}**

(መልካም ሥራ ፊቶቻችሁን ወደ ምሥራቅና ምዕራብ አቅጣጫ ማዞር አይደለም፡፡ ግን መልካም ሥራ በአላህና በመጨረሻው ቀን፣ በመላእክትም፣ በመጻሕፍትም፣ በነቢያትም፣ ያመነ ሰው ገንዘብንም

ከመውደዱ ጋር ለዝምድና ባለቤቶችና ለየቲሞች ለምስኪኖችም፣ ለመንገደኞችም፣ ለለማኞችም፣ ለጫንቃዎችም (ማስለቀቅ) የሰጠ ሰው) ነው፡፡

****

ምስጋና ሁሉ ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የእዝነት መህረትና ሰላም የነብያትና የመልክተኞች መደምደሚያ በሆኑት በሰይዳችን ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

ዘካና ተራ ምጽዋት ተላላቅ ፍሪያማ ጥቅሞች አሏቸው፡፡ ከነሱም መካል አንዱ በረከትና ታላቅ ምንዳ የሚያስገኙ መሆኑ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{يَمْحَقُ اللَّهُ الرِّبَا وَيُرْبِي الصَّدَقَاتِ}

(አላህ አራጣን (በረከቱን) ያጠፋል፡፡ ምጽዋቶችንም ያፋፋል፡፡) እንድሁም አንድህ ይላል፡

{إِنَّ الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ وَأَقَامُوا الصَّلَاةَ وَآتَوُا الزَّكَاةَ لَهُمْ أَجْرُهُمْ عِنْدَ رَبِّهِمْ وَلَا خَوْفٌ عَلَيْهِمْ وَلَا هُمْ يَحْزَنُونَ}

*(እነዚያ ያመኑ፡፡ መልካም ሥራዎችንም የሠሩ፡፡ ሶላትንም ያስተካከሉ፡፡ ዘካንም የሰጡ ለነርሱ በጌታቸው ዘንድ ምንዳቸው አላቸው፡፡ በእነርሱም ላይ ፍርሃት የለባቸውም እነርሱም አያዝኑም፡፡)*

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ደግሞ እንድህ ይላሉ፡ (ከቀናት ባሪያዎች የሚያነጉበት የሆነ አንድም ቀን የለም ሁለት መላእኮች ወርደው አንደኛው ጌታዬ ሆይ! ለሰጠ ተተኪን ስጠው ሌላኛው ደግሞ ጌታዬ ሆይ! እጁን ለማይዘረጋ ውድመትን ስጠው የሚሉ ቢሆን እንጂ)፡፡

ሌላው የዘካና ተራ ምጽዋት ጥቅም ደግሞ ከጤንነት ማግኛ ሰቦቦች አንዱ መሆኑ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (በሽተኞቻችሁን በምጽዋት ፈውሱ፡፡ ገንዘቦቻችሁንም በዘካ ጠብቁ፡፡ መከራን ለመከላከል

በጸሎት ዝግጁ ሁኑ)፡፡ እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ይላሉ፡ (ምጽዋት መስጠት የጌታን ቁጣ ያበርዳል፡፡ መጥፎ አማሚትንም ይከላከላል)፡፡
ዘካ በማህበረሰቡ ዘንድ ሚዛናዊነትን በማረጋገጥና በማህበራዊ ልማት ታላቅ ሚና አለው፡፡ ይህ ጉዳይ ደግሞ ቀጣይነት ያለው የግልም ይሁን የአጠቃላይ ተራ ምጽዋት እንድሁም የመልካም ምግባር ፕሮጀክቶች፣ መጠለያ ለአጡ ቤት መስራትና የሥራ እድል መፍጠር፣ በሰብኣዊ መድህንነት፣ ለቤተሰብ ድጋፍ በማድረግ፣ ለማህበራዊ ልማትና ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ክልሎች መሻሻል የሚያተኩሩ መልካም ተግባራት በሚሉት ዘርፎች በጣም ይሰፋል፡፡
እኛ በአሁኑ ወቅት የመልካም ሥራ መሰረታዊ ትርጉም፣ ትስስርና የማህበራዊ ትብብር፣ የፍቅር መስፋፋት፣ ወንድማዊነት እውን መሆንና የልማት መረጋገጥ እጅጉን ያስፈልገናል፡፡
ጌታችን ሆይ! ሀገራችንን ግብጽን እንድሁም ሌሎች የዓለም ሀገራትን ከመጥፎ ነገር ጠብቅ፡፡ አሚን፡፡